የአዘቦት ቀን የጥዋቱ ፀሎት

“ፕሱኬ ድዚምራ”

ከ“ፕሱኬ ድዚምራ” መጀመሪያ ላይ ይህ ቡራኬ ይባረካል።
“ዓለምን ይሁን ያለው” ጀምሮ እስከ ፀሎቱ ፍፃሜ ድረስ ተራ ነገር መነጋገር ክልክል ነው።
“ዓለምን ይሁን ያለው” የሚለውን በመቆምና በፊት በኩል ያሉትን ሁለቱን ዘርፎች በመያዝ ነው የሚባለው።

ዓለምን ይሁን ያለው

ብሩክ ነው፤ እርሱም ብሩክ ነው፤
የሚናገረውን የሚፈጽም ብሩክ ነው፤
የሚወስነውን የሚተገብር ብሩክ ነው፤
ፍጥረታትን የሚሠራ ብሩክ ነው፤
በምድርም ላይ የሚራራ ብሩክ ነው፤
በፍጥረታቱም ላይ የሚራራ ብሩክ ነው፤
ለሚፈሩት መልካም ዋጋ የሚከፍል ብሩክ ነው፤
እስከ ዘላለም ሕያውና ለዘላለም ነዋሪ የሆነው ብሩክ ነው፤
የሚቤዥና የሚያድን ብሩክ ነው፤
ስሙም ብሩክ ነው፤

ብሩክ አንተ እግዚአብሔር አምላካችን የዓለም ንጉሥ፤
እግዚአብሔር ሩህሩሁ አባት በሕዝቡ አፍ የተመሰገነው፣
በደጋጎችና በባሪያዎቹ ምላስ የሚወደስ የሚደነቅ፤
እግዚአብሔር አምላካችን ሆይ በዳዊት መዝሙር እናመሰግንሃለን፤
በውዳሴዎችና በዝማሪዎች
ታላቅ እናድርግሃለንም፣ እናወድስሃለንም፣ እናደንቅሃለንም፣
እናነግሥሃለንም፤ ለዘላለም ብቻህን ሕያው የሆንከው ንጉሣችን
አምላካችን ስምህን እናስታውሳለን። የተወደስከው ንጉሥ
ለዘላለም በታላቁ ስሙ የተደነቀው፤
ብሩክ አንተ እግዚአብሔር በውዳሴዎች የተሞገስከው ንጉሥ።

በእጁ የያዛቸውን ዘርፎች ይስምና ይለቃቸዋል።

שחרית לחול

פסוקי דזמרה

בתחילת פסוקי דזמרה מברכים ברכה זו.
מ׳בָּרוּךְ שֶׁאָמַר׳ ואילך אסור לדבר בדברי חול עד סוף התפילה.
אומרים ׳בָּרוּךְ שֶׁאָמַר׳ בעמידה, והמתפלל אוחז בשתי הציציות שלפניו.

בָּרוּךְ שֶׁאָמַר

וְהָיָה הָעוֹלָם, בָּרוּךְ הוּא.
בָּרוּךְ אוֹמֵר וְעוֹשֶׂה
בָּרוּךְ גּוֹזֵר וּמְקַיֵּם
בָּרוּךְ עוֹשֶׂה בְרֵאשִׁית
בָּרוּךְ מְרַחֵם עַל הָאָרֶץ
בָּרוּךְ מְרַחֵם עַל הַבְּרִיּוֹת
בָּרוּךְ מְשַׁלֵּם שָׂכָר טוֹב לִירֵאָיו
בָּרוּךְ חַי לָעַד וְקַיָּם לָנֶצַח
בָּרוּךְ פּוֹדֶה וּמַצִּיל
בָּרוּךְ שְׁמוֹ.

בָּרוּךְ אַתָּה יְהוָה, אֱלֹהֵינוּ מֶלֶךְ הָעוֹלָם
הָאֵל אָב הָרַחֲמָן הַמְהֻלָּל בְּפֶה עַמּוֹ
מְשֻׁבָּח וּמְפֹאָר בִּלְשׁוֹן חֲסִידָיו וַעֲבָדָיו
וּבְשִׁירֵי דָוִד עַבְדְּךָ נְהַלְלְךָ יְהוָה אֱלֹהֵינוּ, בִּשְׁבָחוֹת וּבְזִמְרוֹת
וּנְגַדֶּלְךָ וּנְשַׁבֵּחְךָ וּנְפָאֶרְךָ וְנַמְלִיכְךָ
וְנַזְכִּיר שִׁמְךָ מַלְכֵּנוּ אֱלֹהֵינוּ, יָחִיד חַי הָעוֹלָמִים
מֶלֶךְ מְשֻׁבָּח וּמְפֹאָר עֲדֵי עַד שְׁמוֹ הַגָּדוֹל.
בָּרוּךְ אַתָּה יְהוָה, מֶלֶךְ מְהֻלָּל בַּתִּשְׁבָּחוֹת.

מנשק הציציות שבידו ומניחן.